# እጅ መንሻ ይዘው ወደ ወያኔ ሰፈር የገሰገሱ ሰባ ሰገሎች

ከቃል ኪዳን ይበልጣል (ስዊድን)

ይድረስ ለመድኅን ራዲዮ ዝግጅት አባላትና ታዳሚዎች ይሄንን የይድረስ መልዕክቴን ወደ ራዲዮ ጣቢያው ለማድረስ የብዕር መንገድ የጀመርኩት ገና ዛሬ ነው። የመድኅን ራዲዮ ጣቢያ ከተከፈተ ጊዜ ጀምሮ የሚተላለፈውን መልዕክት በማዳመጥ የመጀመሪያው ሰው ነኝ ላማለት የሚያስችል ሙሉ ድፍረት አለኝ። በተለይም ጊዜን ገንዘብን እውቀትን አስተባብራችሁ ለወገን ፍቅርና ሰላም መቆምን የመሰለ የሰው ልጅ ፀጋ እንደሌለ አምናችሁ ለወገኖቻችሁ የምታስተላልፉት ዝግጅት ከልብ አስደስቶኛል። ከሀገር ርቃችሁ ሀገር ውስጥ የሚገኙ ወገኖቻችሁን ጭቆናና የጨቋኞችን ምድራዊ ስቃይ ለማስወገድ የምታደርጉት አስተዋጽኦ ለተተኪው ትውልድ በአኩሪ ታሪክነቱ የሚተላለፍ መሆኑን ስገልጽላችሁ የሚሰማኝ ደስታ ወደር የለውም። እኔ በእድሜዬ ሽምጊያለሁ፤ የሀገሬን ጉዳይ ከማወቅና ያውኩትንም ከመተግበር አንጻር ግን ገና ልጅ ነኝ ማለት እችላለሁ። የመድኅን ራዲዮ ጣቢያ ተከፍቶ በሳምንት ሁለት ቀን ሐሙስና እሁድ የሚያስተላልፈውን ሀገራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በመከታተሌ ግን ከልጅነት ተላልፌ ሀገርን ወደ ማወቅ ጉልምስና እየተለወጥኩ ነው ማለት እችላለሁ። በተለይም የራዲዮ ጣቢያው ባልደረባ ቀርሜሌዎስ ወያኔ የሚፈነጭባትን ኢትዮጵያንና በወያኔ የድንቁርና የጎሣ አገዛዝ የሚሰቃየውን ሕዝብ ብሶትና ምሬቱን እየበረበረ የሚሰጠውን መረጃ ስሰማ አይኔን እንባ ልቤን ቁጭት ይሞላዋል። ስለዚህም እሱንም ማመስገን እፈልጋለሁ። ቀርሜሌዎስ በሚያቀርብላችሁ ትንታኔ በሚልክላችሁ ዜና በመርካታችን ይህንን ግለሰብ ደካሙን ይሚያበረታታ አእምሮዉን የሚያሰፋ የወዳጅ ስጦታ ልናበረክትለት አስበናልና በላኩላቸሁ አድራሻዬ በኩል የእሱን አድራሻ እንድትልኩልኝ በሀገራዊ ልጅነት ፍቅር እጠይቃለሁ። እናንተ የመድኅን ራዲዮ ዝግጅት አቅራቢዎች መድኅን ድርጅትን የመሰረቱ ሁሉ በመሰረቱት ድርጅት አማካኝነት እየታገሉ ሊያታግሉን ቃል ገብተው ለዓመታት ሲንቀሳቀሱ እንደነበር አውቃለሁ። በእንቅስቃሴአቸውም መካከል እነሱ ብቻ ሳይሆኑ ሕዝብ እንዲተባበር፣ ከጭቆናም አገዛዝ እንዲላቀቅ ገንዘባቸውንና እውቀታቸውን ከጊዜ ጋር አቀናጅተው ከሀገር ብንርቅም የወገናችን መጨቆንና መረገጥ ሀገር ውስጥ ያለን ያህል ይሰማናል ብለው ኢትዮጵያና ሕዝቧ ከወያኔ አገዛዝ ነፃ እንዲወጡ ነፃነትን አውጀው እንተባበር ሲሉን እንደነበር አይዘነጋም። ነገር ግን እነዚያ እንተባበር ሲሉን የነበሩ ወገኖቻችን ዛሬ ተለያይተው በማይሆን ተግባርና ከማይሆን የጎሳ ባላባትና የፖለቲካ ባላምባራሶች ጋር ገጥመው እነሱም የሥልጣን ማደጎ ፈታውራሪ ሊባሉ ወያኔ በቀደደው ቦይ ውስጥ ለመፍሰስ መንቀሳቀሳቸውን ስንሰማ እኔና ለሀገርና ለሕዝብ አንድነት የምናለቅስ ወዳጆቼ ለተለያያችሁት ሳይሆን ቃልኪዳኑ ለማይከበርለት ወገናችን በብዙ አልቅሰናል። እኛ እዚህ ስናለቅስ ከመድኅን ተገንጥለው የኮበለሉት አባላት ወደ ወያኔ ገስግሰው 'እነሆ ለአንተ ሥልጣን እጅ ሰጥተናል አንተ በአንተ በጎ ፈቃድ የምትለውን በለን ብለው የፖለቲካ ሳጥናቸው ውስጥ የእጅ መንሻ ስጦታ ይዘው መቅረባቸው ይበልጥ አስገርሞኛል። ወያኔም በተለመደው የመነጣጠልና አንዱን በአንዱ የመለጣጠፍ ተግባሩ አስቆ በሚያስለቅሰው ፖለቲካው በፊቴ ሞገስ ለማግኘት ከመጣችሁ የምላችሁን ትፈጽሙ ዘንድ ቃል ገብታችሁ ወደ ተነሳችሁበት ተመለሱ ብሎ የድርጅት እውቅና ሰጥቶ እንደመለሳቸው ስሰማ የስማሁትን ማመን አቅቶኝ ሕመም ቢጤ እንዲሰማኝ አድርጎኛል። በኮ/ል ጎሹ ወልዴ የሚመራው ከመድኅን ተገንጥሎ የወጣው ቡድን በእውነት ከወያኔ ጋር ተስማምቼ እሰራለሁ ወይም እታገላለሁ ብሎ ከሆነ ይህ አካሄዱ የፖለቲካ ብስለት የጎደለው መስሎ ይታየኛል። ይቅርታ ይደረግልኝና ባልደረባችሁ ቀርሜሌዎስ በአንድ ሀተታው ስለአድርባይነት የጠቀስውን ልዋስና ልጠቀምበት። የዛሬን አያድርገውና ታላቋን ሩሲያን ለመውረር በአውሮፓ ኃያልነትን ተጎናጽፈናል ሲሉ የነበሩ ጦረኞች መድፍና ታንክ በበረህ ምድር እያስጓሩ ወደ ሞስኮ ከተማ ተቃርበው ነበር። በጊዜው ስታሊን የጦሩን ከፍተኛ ጄነራሎች ሰብስቦ ሩሲያን ከወራሪዎች እንዲታደጓት ንግግር አደረገላቸው። እናንተ የጦር እውቀት ያላችሁ ጄኔራሎች ታላቋ ሩሲያ አባት ሀገራችን ጠላቶቿ ሊደፍሯትና የመጨረሻ ውድቀቷን ሊመለከቷት እነሆ ወደ ሞስኮ እየገሰገሱ ናቸው። እኛ ደግሞ ይህንን የእብሪተኞችንና የወራሪዎችን ክንድ ለመመከት እንደምንችል በእናንተ ላይ ጽኑ እምነት አለኝ። ወደ ውጊያው መስመር ለመግባት የቀረን ጥቂት ስዓት ነው በእነዚህ ጥቂት ሰዓቶች አንድ ሥራ መስራት አለባችሁ። ውጊያውን ብናሸንፍ ሙሉ በሙሉ ደስተኞች እንሆናለን። በውጊያው ብንሸነፍ ስልታችንን ለውጠን እንደገና ልንዋጋ እንችላለን። ፈጽሞ መዋጋት የማንችለው አድር ባዮችን እንዋጋለን ብለን ስናስብ ብቻ ነው። አድርባዮችን እንዋጋለን ብንል እንኳን ይህ ውጊያ የሚካሄደው ከፊትና ከኋላ ባለ እሳት መካከል የመቆም ያህል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። የዚህ ዉጊያ አደገኛነቱ ወደፊትም ወደኋላም እንቀሳቀስ ብንል እሳቱ ይበላናል። አድርባይ ማለት ከፊትም ከኋላም የሚገኝ እሳት ስለሆነ ከጦርነቱ በፊት አድርባይነትን ለማስወገድ መላ ፍጠሩ። ነበር ያላቸው ሲል ቀርሜሌዎስ በሀተታው አድርባይነትን አሳምሮ ገልጾታል። እኔ እንደ ቀርሜሌዎስ ልተነትነው ቀርቶ የሰማሁትን መልሼ ለማስረዳት ስላልቻልኩ እሱ ያለውን ለመግለጽ የሞከርኩት አድርባይ የሚለውን ቃል ብቻ ነው። አድርባይነት መጥፎ የትውልድ በሽታ ነው። አድርባይነት ከቤተሰብ የሚያራርቅ፣ ከድርጅት የሚያጣላ፣ ከቃል ኪዳን የሚያስፈነግጥ፣ እንደ ጅብጥላ ለሰው ሕሊና የሚከብድ፣ ሳያራምድ አድርሶ እያስሮጠ ግብን የማያስጨብጥ ታላቅ የአባለዝር በሽታ ነው። አድርባይነት በበራብት የሚጨልም ሳይበላ የሚያጠግብ የሚመስል እየተበላ የሚያስርብ ሆድ የሚያሳብጥ በሽታ ነው። እኔ

ባለሁበት ሀገር ታምሞ ነፍሱ ከተለየችው ኢትዮጵያዊ ሳይታመም መድሐኒት ፍለጋ የሚባዝነው አድርባይ በየቀኑ ቁራጭ ቁራጭ ሞት ለመሞት የሚያጣጥረው ለትክክለኛ ነፍሱ መድሐኒት ስላልተገኘለት ነው። የአስከሬን ሳጥን ለማሰራት የሞተ አካሉ ላይ የሚያርፈውን ጨርቅ ለማሰፋት ችግር ሲፈጥርም ይታያል። እኔ ባለሁበት ሀገር የአድርባይነት ጋዝ የያዘው ስለሚበዛ ወያኔ ደጅ መቅረዙን ለማብራት ግራ በመጋባቱ አንድም ሆዱን ለመሙላት ወይም ከውጭ ሀገር የመጣ ፖለቲከኛ ተብሎ ስልጣን ለመቀራመት ሲል በአድርባይነት የሚታመመው ይበዛል። እውቀትም እምነትም ድፍረትም ገንዘብም ሳያጡ ከወያኔ ጉያ ለመሸሸግ ለወያኔ እጅ መንሻ የሚያቀርቡ የፖለቲካ ሰባ ሰገሎች ሆነው የፖለቲካ ሳጥን ተሸክመው ከሰለጠነው ዓለም ቃል ኪዳናቸውን ጥለው ክብራቸውን ትተው ሕዝብ ሕዝብ ለማይሸት ስልጣን ከሩጫው ማስተኮሻ ሥፍራ ሩጫቸውን ወደማያገባድዱበት ወያኔ ሜዳ ላይ ለመሮጥ ሰውነታቸውን ሲያሟሙቁ የሚውሉ ይበዛሉ። ወደ ተነሳሁበት ነጥብ ልመለስና መድኅን ለሁለ በመከፈሉ አንደኛው ቡድን ተነጥዬ ወጥቻለሁ ብሎ ወደ ወያኔ ሰፈር ያለቦታው የሮጠበት ምክንያት ምን እንደሆነ ከዚህ በፊት በራዲዮ ጣቢያው በኩል መግለጫ ስለተሰጠበት ያንን ነጥብ ማንሳት አልፈልግም። አሁን ለማወቅ የፈልኩት በኮ/ል ጎሹ ወልዴ ይመራል የተባለው ቡድን ማንን ይዞ ነው ወያኔን በምርጫ ሊያሸንፍ ወደ ምርጫ ኮሚሽን ምዝገባ ቢሮ ጎራ ያለው? ሊመዘገብ የተደፋፈረበት ሚስጥር ግልጽ እንዲሆንልኝ እፈልጋለሁ። ኮ/ል ጎሹ እንደዛሬው የመድኅንን ሁለተኛ ቁጥር ሳይጨብጡ ወያኔ የሚወድቀው በጠመንጃ ስለሆነ ታንከኛው፣ መድፈኛው፣ አየር ማቃወሚያው፣ መገናኛው፣ መሀንዲሱ፣ ባህረኛውና አየር ሀይሉ የሻዕቢያን ምሽግ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ የተዋረደ ክብሩን በክብር ለመለወጥ እንዲነሳና እንዲንቀሳቀስ ጥሪ አድርገው እንደነበር አስታውሳለሁ። ተነስ የተባለው ተኝቶ ተንቀሳቀስ የተባለው ቆሞ የሞተው ሞቶ የለወንጀሉ ርሀብተኛ በሆነበትና ጎሰኞች የሚሰሩትን በቀል ፈጽመውበት ጉልበቱ መክኖ ቤት ሙሉ ለቅሶ ሀገር ሁሉ ርሀብ በሆነበትና ጎሰኞች በሚሰሩት በቀል አዳዲስ በቀሎችን ለማካሄድ ችግኝ መትከያ ሜዳ ጠርገው ጣራ ከድነው በተቀመጡበት ስዓት አንድነትን ንዶ ቃልኪዳንን ደምስሶ እንደትላንቱ ሳይሆን እንደዛሬው ከዛሬው ጨቋኞች ጋር መቀላቀል ይሻላል ብሎ ወያኔ ሰፈር የፖለቲካ ሰባ ሰገል ሆኖ መቅረብ ለምን አስፈለገ? እኔ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያነበብኩትን የሰባ ሰግሎች አካሄድ ለወያኔ የፖለቲካ ሳጥን ይዘው ከሄዱት ጋር ሳስተያየው እነዚህ ወደ ጨለማ እንዚያ ወደ ብርሃን ማምራታቸውን ያሳየኛል። በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ሁለት ከምዕራፍ አንድ እስከ አስራ ሁለት ያለው እንዲህ ይነበባል።

> *እየሱስም በይሁዳ ቤተልሄም በንጉሱ በሄርዶስ ዘመን በተወለደ ጊዜ እነሆ ስብአ ሰገል የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው ኮክቡን በምስራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምስራቅ ወደ እየሩሳሌም መጡ። ንጉሥ ሄርዶስም ሰምቶ ደነገጠ። እየሩሳሌምም ሁሉ ከእርሱ ጋር የካህናትም አለቆች የህዝቡን ግሮች ሁሉ ሰብሰበው ክርስቶስ ወዴት እንዲወሰድ ጠየቃቸው። እነርሱም አንቺ ቤተልሄም የይሁዳ ምድር ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሺም ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና። ተብሎ በነቢዩ እንዲህ ተጽፏልና በይሁዳ ቤተልሄም ነው አሉት። ከዚህ በኋላ ሄርዶስ ሰብአ ሰገልን በስወር ጠርቶ ኮኮቡ የታየበትን ዘመን ከእነርሱ  በጥንቃቄ መርምሩ ባገኛችሁትም ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንግሩኝ አላቸው። እነርሱም ንጉሡን ሰምተው ሄዱ። እነሆ በምስራቅ ያዩት ኮኮብ ሕፃኑ ባለበት ላይ መጥቶ እስኪቆም ድረስ ይመራቸው ነበር። ኮኮቡንም ባዩ ጊዜ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማሪያም ጋር አዩት። ወድቀውም ሰገዱለት። ሣጥናቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና እጣን ከርቤም አቀረቡለት*

ይላል። ከክርስቶስ መወለድ ሁለት ሺህ ዓመት በኋላ በኢትዮጵያ ምድር የፖለቲካ ሰይጣን ተወልዶ ከመድኅን የተነጠሉ የፖለቲካ ሰባ ሰገሎች ለተወለደው ወያኔ ለተባለ የፖለቲካ ሰይጣን እጅ መንሻ ይዘው መጓዛቸው የሄርዶስንና የወያኔን ዳቢሎሳዊ ብቀላ ለማስተናገድ መሆኑ በጣም ያስገርመኛል። በአንድ በኩል እጽናናለሁ ሄርዶስ የላካቸው ሰባ ሰገሎች የዓለምን ብርሃን አይተው ለሄርዶስ መልስ ሳይሰጡ በዚያው ቀርተዋልና የያኔዎቹን ሰባ ሰገሎች ስጽናናባቸው የዛሬዎቹን የተገንጣዩ መድኅን ሰባ ሰገሎች ወደ ዲያብሎስ የፖለቲካ ሳጥን ውስጥ እጅ መንሻ የዘው በመዝለቃቸው አፍርባቸዋለሁ። ምክንያትም ቃል ኪዳንን ህብረትንና ወገናዊነት የሌለውን በፍቃድህ ተቀበለን እንጂ ያዘዝከንን ልንሆን ጥሪህን ሰምተን ወዳጆቻችንን ክደን የምርጫ ገፀ በረከት አምጥተንልሃል ብለው የፖለቲካ ሰባ ሰገሎች በመሆናቸው የዘመኑ አስደናቂ የፖለቲካ ሰባ ሰገሎች ሆነውብኛልና። የዘላለምን ብርሃን ለመፈለግ ትናንት ቃል ኪዳን ገብተው የሄርዶስን ምኞትና ጥፋት ሊያመክኑ ድምጻቸውንና ጥሪያቸውን እያሰሙ አሜሪካን አውሮፓ ያሉ ወገኖቻችን ዛሬ ደግሞ የሄድሮስን ምኞት ለማሳካት አዲስ ወደ ተወለደው የፖለቲካ ሰይጣን የመነጣጠልን እጅ መንሻ የዘው መቅረባቸው እጅግ ያስገርማል። እነዚህ ወግኖቻችን እውቀታቸውንና ለሕዝብ አለን የሚሉትን መልካም ቁም ነገር ትተው የማይታመነውን ወያኔ አምነው ጊዜያቸውን ለህገራቸውና ለሕዝባቸው ጉዳይ ያዋሉ ወገኖች ያሉበት የመድኅን ድርጅት በቃሉ ታምኖ  ሊከፈል የሚገባውን ዋጋ እየከፈሉ ባሉበት ሰዓት ስለምን ሕይወትን ወደ ሞት እምነትን ወደ ክህደት ህብረትን ወደ መነጣጠል የሚለውጥ ተግባር ለመፈጽም እንደተነሳሱ ሳስበው በሀገሬ ልጆች የመተማመን ጉድለት እጅግ እጨነቃለሁ። ሄርዶስ ሰባ ሰገልን በድብቅ ጠርቶ የሚገደለውን ሕፃን ፈልጉ እንዳለው ስለምን  በኮ/ል ጎሹ ወልዴ የሚመራው ቡድን ወያኔ በስውር አደራጅቶታል እስኪባል ድረስ አዲስ አበባ ድረስ ተጉዞ እጁን ሊሰጥ የፈለገበት ምክንያት ፈጽሞ ግልጽ

አልሆነልኝም። ለወያኔ ፖለቲካ መድኅንን ጭዳ ለማድረግ ታስቦ ከሆነ ይህ በሁላችን ዘንድ የሚታመን ተግባር ሊያመጣ ይችላል ብዬ አላስብም። በቅርቡ አዲስ አበባ ገብቶ መግለጫ የሰጠው የመድኅን ተገንጣይ ቡድን በመግለጫው ላይ "ትግሉ ወዳለበት የትግል ሜዳ ወደ ሚገኝበት አደጋው እርግጥኛ ወደ ሆነበት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ተሰልፎ መታገልን የመሰለ ሀቀኛ አኩሪ ቆራጥና ጀግና አድራጎት የለም። ሕጋዊው የመድኅን አመራር በሀገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ መሰረት ሕጋዊ ሰውነት በማግኘት በእናት ሀገሩና በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ተግኝቶ ድርጅታዊ ስራውን ለመጀመር የምዝገባ ሥርዓት እያሟላና ሌሎች ሁኔታዎችን እያመቻቸ ይገኛል" ብሏል። እርግጥ መድኅን ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ወደ ትግሉ ሜዳ ይገሰግስ ይሆን? ለትግሉ በቁነት ያላቸው አባላት አዘጋጅቶ ከሆነ የሠላሙ ትግል መልኩን ለወጠ ማለት ነው። ምክንያቱም ኮ/ል ጎሹ ከዚህ በፊት ያሰሙትን የተነስ፣ የታጠቅና የተዋጋ ጥሪ አሁን አያስፈልግም በለው በሰላም ለመታገል ወስነዋልና ይህ ውሳኔያቸው ትግሉ ወዳለበት የትግል ሜዳው ወደሚገኝበት ቅራጥና ጀግና በመሆን ለመታገል ከሀገር እርቆ ተቀምጦ በጦር ሜዳ ውጊያ ላይ እንዳሉ በማስመሰል ደጉን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከማታለል ይልቅ ትግሉ ወዳለበት መቀላቀል ይበጃል የሚል እርስ በርሱ የተጫረሰ መግለጫ ሰጥቷልና። መድኅን እንዴት ብሎ ነው ሀገር ውስጥ ገብቶ ከወያኔ ጋር ሊታገልና ሊያሸንፍ የሚችለው? ይህንን ከኮ/ል ጎሹ ወልዴ የበለጠ የሚያውቅ ሰለሌለ መግለጫውን ከምን ተነስተው እንዲያ ሊሉ እንደቻሉ ሌላ መግለጫ ቢያስነብቡኝ ፍላጎቴ መሆኑን እገልፃለሁ። አሁን አሁን እንደገባኝ ግን ወያኔን ለመጠጋት ሰላም የሚለው ዘዴ ዋንኛው መሆኑን ነው። ሁለተኛው ደግሞ መድኅን ለምን ወደ ወያኔ ተጠጋ እንዳይባል ወይም ወያኔን ተደግፎ ስልጣን ለመያዝ ያቀደው ስልት ነው እንዳይባል የራሱን ሰዎች ጠረኛ አድርጎ እሱ የሰላም አለቃ በመምሰል የፈለገውን ስልጣን መጨበጥ የሚችለው በዚህ መንገድ መስሎም ይታየኛል። ይሄንን ዘዴ ባይጠቀም ኖሮ ወደ ወያኔ ከተማ የምርጫ ኮከብ እየመራው ሄዶ ወያኔ ሰፈር አይገኝም ነበር።

ለመሆኑ ወያኔ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶች እያሰረና እየገደለ የሚቀልድባቸው አባሎች ፊት ለፊቱ እያሉ ይህ አገር አቋርጦ ወያኔ ሰፈር የገባው በኮ/ል ጎሹ የሚመራው መድኅን የወያኔ ወዳጅ ልሆን እችላለሁ ብሎ ማሰቡ የፖለቲካ እውቀቱን አያሳንስበትም የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ይመስለኛል። ጥያቄውም ጠላቴ ወዳጄ ሆኖ ድምፄን ሰምቶ ስለመጣ በፍፁም ልቤ አምኜ ተቀብዬዋለሁ የሚለውን ሳይሆን በፖለቲካ ግሌቶን ጨለማው ቤት ውስጥ የአንገቱን ስሮች በጥሶ መስዋዕት የሚያደርግ ምላሽ የሰጥዋል በዬ ነው የማስበው። በሌላም በኩል ከመድኅን ራዲዮ ዝግጅት በኩል እንደሰማሁት አናሳውና ከመድኅን ተገንጥሎ የወጣው ቡድን ተወካዮች አዲስ አበባ ደርሰው በ1997 ዓ.ም የምርጫ ተወዳዳሪ ለመሆን ያስገቡት ማመልከቻ በወያኔ የፖለቲካ ልጆች ተቀባይነት እንዲያገኝ ማስተካከል ያለባቸውን ጉዳይ ተንግሯቸው የድርጅት መሀተማቸውን ለውጠው ወያኔ ወደ ሚፈልገው የምረጡኝ ፖለቲካ እንዴት መቅረብ እንዳለባቸው ተነግሯቸው የተባሉትን አስተካክለው ወደ ላኳቸው አለቆቻቸው ተመልሰው ሪፖርት ማቅረባቸውን ነው። በጠመንጃ እንጂ በሰላማዊ መንገድ ወያኔ አይንበረከክም ያሉ ወገኖቻችን ሀሳባቸውን ለውጠው በሰላማዊ መንገድ መታገልን መምረጣቸው ክፋት የለውም። ሰው የፈለገውን የትግል አቅጣጫ መምረጡ ዲሞክራሲያዊ መብቱ ስለሆነ ማንም ብዚህ ሂድ በዚያ ተመለስ ሊለው አይችልም። ትክክለኛ ያልሆነ መንገድ ሲመርጥ ግን አይጠቅምህም አያስኬድህም ብሎ ሀሳብ መስጠት የወዳጅነት እንጂ የጠላትነት ወይም የምቀኝነት ትርጉም ሊሰጠው አይችልም። እኔም የእነ ኮ/ል ጎሹ አካሄድ በተጠረገው ጎዳና ላይ የሚሄዱ የመንገድኞች ጉዞ አልመሰለኝም በማለት ጉዟቸው የወያኔ የፖለቲካ ሰባ ሰገሎች ጉዞ ሆኖብኛል ለማለት የደፈርኩት እነ ኮ/ል ጎሹ ወያኔን በተጠጉ ቁጥር የኢትዮጵያ ሕዝብ አጋሬ አለኝታዎቼ ሲላቸው ስለነበረ በሕዝቡ የጥርጣሬ ብቻ ሳይሆን የተስፋ ማስቆረጥ በር መክፈታቸውን አላስተዋሉም ብዬ ነው። አንድ የነበሩ ተነጣጥለው እልህ አስጨራሹን ትግል እዳር አደርሳለሁ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው እላለሁ። የራሺያ መፈራረስ ሊመጣ የቻለው አንዱ ለሀገርና ለሕዝብ ሲያስብ ሌላው ከፍርስራሹ ውስጥ የሚገኘውን ስልጣን ለመያዝ በመጎምዥት በቻ ነው። የተባበሩ ጀርመናውያን የመለያየትን ግንብ አፍርሰው አንድ ሆነዋል እንጂ ተነጣጥለው አንድነት አልፈጠሩም። በሴራ ገመድ የተጠላለፉ እንደ ወያኔና ሻዕቢያ አንድ ጠመንጃ ላይ ሁለት ጣቶቻቸውን አስገብተው ትኩሰው ውጤት ሲገኝ በአንድ ጠመንጃ ሁለት ጣት ሳይሆን በአሥር ጠመንጃ አንድ ጣት ብቻ ማረፍ አለበት ብለው እንደ ሌቦቹ እስኪሰርቁ ተስማምተው ከሰረቁ በኋላ ክፍያው ላይ እንደተጣሉት ውጤቱ የኔ ነው በሚል የረጋውን ሰላም በጥቅም ጦርነት ለውጠው የብዙ ሺህ ሰዎች ነፍስ እንዳጠፉት አይነት መለያየት ይመጣል። መድኅን እንደዚህ ያለ መከፋፈል ከመከፋፈልም አልፎ ለወያኔ የእጅ መንሻ የፖለቲካ ሳጥን ይዘው የሚገሰግሱ አባላት ከውስጡ ይወጣሉ ብሎ ለመናገር ቀርቶ ለማሰብም ይከብደኝ ነበር። አሁን ግን ያልታሰበው ሆኗል።ወያኔም በመድኅን መከፋፈል ተደስቷል። ጠላት በወዳጆቹ መነጣጠል ሲስቅ ከማየት የበለጠ አሳፋሪ ሞት የለምና ሰዎች ያልፋሉ ታሪክና ሀገር ፀንተው ስለሚኖሩ ወደ ወያኔ የተጓዘው የኮ/ል ጎሹ ቡድን ወደ ሀገራዊ ታሪክ ፊቱን መልሶ መድኅን አንድ ሆኖ በባእድ ሀገር የምንኖር ኢትዮጵያውያን ጆር የአንድነት አዋጅ እንዲሰማ ይህ መልእክቴ ለተገነጠለውም ባለበት ፀንቶ ለቆመውም መድኅን ይድረስኝ እላለሁ። መልእክቴ ለሁሉም ደርሶ ወደ ወያኔ የገሰገሱ የፖለቲካ ሰባ ሰግሎች ሄርዶስ የላካቸው ሰባ ሰገሎች እንዳደርጉት ብዚያው በወያኔ ሰፈር ሳይሰወሩ ወደ መሰረታዊው መድኅን ተመልሰው ሰላምናን ሕብረትን እኔነትንና ስለሌላው አይገደኝም ማለትን ትተው የምስራች እንዲያሰሙን በመጠየቅ ይድረስ ያልኩትን መልእክቴን በዚሁ እዘጋለሁ።

የዘወትር አድማጫችሁ
ቃል ኪዳን ይበልጣል